## *ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ መፅሐፍ ያየሁት*
## *(እውነትም የነፃነት ጎህ ቀዷል)*

*614 ገፆች:: መፅሐፉ የተጀመረውና የተፃፈው በቃሊቲ ማረፊያ ቤት:: የተጠናቀቀው ግንቦት 13፣ 1998ዓ.ም ከምሽቱ 5:00 ሰዓት በቃሊቲ ማረፊያ ቤት:: ፀሐፊውም በግንቦቱ ምርጫ ወደ መድረክ ብቅ ብሎ በአጭር ጊዜ ከዜሮ መቀመጫ ወይም ስልጣን አዲስ አበባን ለመቆጣጠር፣ በተወካዮች ምክር ቤት ከመቶ በላይ ወንበሮች ለማግኘት የበቃው የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ እና የቀስተ ዳመና ፓርቲ አመራር የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ ናቸው:: ይህን ትልቅ የፖለቲካ ድል እምቢኝ ብለውና ሁሉንም ወይንም ምንም በሚል መፈክር ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ስርዓቱን ገርስሰው ስልጣን ለመያዝ በመንቀሳቀስ ተጠርጥረው በሀገሪቱ ህግ መሰረት ክስ ተመስርቶባቸው በፍርድ ሂደት ላይ ይገኛሉ:: ይህም በመሆኑ ዛሬ ከተወሰኑ ሌሎች የቀድሞ አመራር ጓዶቻቸው ጋር ሆነው በቃሊቲ ማረፊያ ቤት ናቸው:: እንግዲህ ከፍ ሲል እንደጠቀስኩት ይህን ወፈር ያለ መድብል የሰጡን በዚህ መልኩ ሊገኙበት ከቻሉት ቃሊቲ እስር ቤት እንደሆነ በመጀመሪያው ገፅና በመጨረሻው እራሳቸው ይነግሩናል::*

*በእርግጥም መከሰስ፣ ተጠርጥረውም ሆነ እጅ ከፍንጅ ተይዘው በቁጥጥር ስር መዋል፣ ወይም በህግ ጥላ ስር ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ መቆየት (በስህተትም ተወንጅለው ይሁን በእውነተኛ ጭብጥ ላይ በተመሰረተ ተከሰው) የትም ያጋጥማል:: ምክንያቱም የህግ የበላይነት በሰፈነበት ወይም እንደ እኛ እንዲሰፍን ጥረት ባለበት ሀገር ማንም ግለሰብ (በህዝብ ይወደድ ወይም ይጠላ፣ ምንዝር ይሁን መሪ፣ ፕሮፌሰር ይሁን መሐይም) በህግ ከመጠየቅና ለህግ ከመገዛት ውጭ መሆን አይችልምና:: ዋናው ጥያቄ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ዜጋ የቀረበበትን ጭብጥ በተመለከተ በእኩል ነፃነትና ተሰሚነት ተከራክሮ ፍትህ የሚያገኝበት የፍርድ ሂደት መኖሩ ወይም አለመኖሩ ነው:: በተያያዥ ሊነሳ የሚገባው ሌላ ጥያቄ ደግሞ በቁጥጥር ስር ከመዋል አንስቶ በማረፊያ ቤት ያለ ቆይታ ሰብዓዊና ዜግነታዊ መብትን የጣሰ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው:: በሁለቱም ደረጃ ዶ/ር ብርሃኑን እና ጓዶቻቸውን አስመልክቶ የምናገኘው ምላሽ «አዎ ፍትሕ የሚገኝበት የፍርድ ሂደት አለ፣ አዎ ቆይታቸውና አያያዛቸውም ሰብዓዊነትንና ዜግነታዊ መብትን ያከበረ ነው» የሚል ነው:: ይህ ለመሆኑም ዶ/ር ብርሃኑ «የነፃነት ጎሕ ሲቀድ» በሚለው መፅሐፋቸው በኩል ምስክርነታቸውን ሰጥተውናል:: አለፍ ሲልም በዚህ ረገድ ይሰነዘሩ የነበሩ ጥርጣሬዎች ወይም ወቀሳዎች ከፍ ሲል ፖለቲካዊ ድጋፍን ለማግኘት የተፈበረኩ የፕሮፖጋንዳ ገለፃዎች ዝቅ ሲል ደግሞ እውነቱን ካለማወቅ የመነጨ የዋህ ግምት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው:: በጭብጥ አስደግፌ በአጭሩ ላብራራ::*

ዶ/ር ብርሃኑ እና አብረዋቸው በቁጥጥር ስር የሚገኙ ተከሳሾችን በተመለከተ ከመጀመሪያው እለት አንስቶ ብዙ ተብሏል:: የጥቂት ቀናት ሀሜታውን ትቼ ተደጋግሞ የሚያጋጥሙ ዋና ዋና የወቀሳና የተቃውሞ ነጥቦች ልጥቀስ:: አንደኛ፣ ተከሳሾቹ የህግ እስረኛ ሳይሆኑ በእምነታቸው የተነሳ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ናቸው:: ሁለተኛ፣ ታስረው የሚገኙበት ሁኔታም እጅግ ዘግናኝ የሆነ አያያዝ ያለበት በመሆኑ ከዘመድ ጋር መነጋገርና የፈለጉትን ማንበብና መፃፍ ይከለከላሉ፤ የታሰሩትም እጅግ በተጣበበና በተፋፈገ ክፍል ውስጥ ነው:: ሶስተኛ፣ ይህም በመሆኑ በበቂ ደረጃ ለመንቀሳቀስም ሆነ ለመተኛት ካለመቻላቸውም በላይ ብዙዎቹ ለተለያየ በሽታ ተዳርገዋል የሚሉት ይገኙበታል:: የመጨረሻውን ሶስተኛ ነጥብ እውነተኛነት ለማስረገጥም በዋቢነት ተደጋግሞ የሚቀርበው ይህን መፅሐፍ ያበረከቱልን የዶ/ር ብርሃኑ የመተንፈስ ችግር ተጠቂ ሆኖ ለሆስፒታል አንድ ሰሞን መብቃት ነው:: አንድ በአንድ እንመልከተው::

## የፖለቲካ ወይስ የህግ እስረኛ?

አንድ ሰው የፖለቲካ እስረኛ የሚባለው የፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም መሪ በመሆኑ በህግ መታሰር ወይም መጠየቅ የለበትም ከሚል አይደለም:: ይልቁንም የፓርቲ አባል በመሆኑ ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ የተለየ እምነት በመያዙ ብቻ እንዲታሰር ከተደረገ ነው:: የዶ/ር ብርሃኑና ጓዶቻቸው ጉዳይ ከዚህ ውጭ ለመሆኑ ማስረጃው ደግሞ ሀ/ ይህንን አባልነትና እምነት ይዘው ብቻ ሳይሆን በአደባባይ ገልፀውና እንደ አማራጭ አቅርበው «ምርጫ» ተወዳድረዋል፣ ተንቀሳቅሰዋል፣ ባሸነፉባቸው ቦታዎችም እንዳሸነፉ በኦፊሴል ታምኖላቸዋል:: ከስልሳ በላይ ከሆኑት የድርጅታቸው መሰል አመራሮች ውስጥም ያልታሰሩ ግን ዛሬም ይህን እምነት ይዘው የሚንቀሳቀሱ ከአርባ በላይ ግለሰቦችና ከመቶ በላይ የፓርላማ አባላት አሉ:: ታዲያ እነዚህ በምን ምትሐት ተረፉ? የተባለው ቢሆን ኖሮ ይህንን ማድረግ አይቻላቸውም፣ ይቻለናል ብለው በድፍረት ሞክረው ከነበረ ደግሞ ከመታሰር የሚያድናቸው ምንም የለም:: ይህንንም ውሸት ብንል እንኳን የማናልፈው ሌላ እውነት አለ:: ይህም ለ/ዶ/ር ብርሃኑ የታሰሩት የተለየ ፖለቲካዊ እምነትን በማራመዳቸውና በመግለፃቸው፣ ይህም መንግስትን ስላስፈራው ወይም ስለጎዳው ካደረጉት በላይ በአደባባይ መግለፃቸውን እንዳይቀጥሉ ለማድረግ ሲባል ከሆነ፣ ከታሰሩበት እስር ቤት ውስጥ ሆነው ይህንኑ የተለየ የፖለቲካ ሀሳባቸውን በመፅሐፍ መልክ ሊሰጡን መቻል አልነበረባቸውም:: አሊያ ከማረፊያ ቤት ውጭ ሆነን የያዝነውን የተለየ እምነት መግለፅ እንዳንችል የታፈንን ሁሉ ይህን ነፃነት ለማግኘት ማድረግ ያለብን ቃሊቲ መውረድ ሊሆን ነው:: የዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ እሳቸውም ሆኑ አብረዋቸው በማረፊያ ቤት የሚገኙ ጓዶቻቸው የህግ እንጂ የፖለቲካ እስረኛ ያለመሆናቸውን የማይካድ እውነት የሚያሳይ ህያው ምስክር ነው:: ተገድደው ፃፉት ካላልን በስተቀር::

## የታሳሪዎቹ አያያዝና የዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፍ:- የሚባለውና እውነቱ

እንደጠቀስነው ዶ/ር ብርሃኑ እና ጓዶቻቸው በአማካይ ከመቶ በላይ የሆነ ታራሚ ባለበት ክፍል ታፍገው ያሉ እንደሆነ ሲነገር እንሰማለን፡፡ በዚህ የተነሳም ዶ/ሩ ለመተንፈስ ችግር ተጋለጡ ተብሎ በእርግጥም ህክምና ሲደረግላቸው አስተውለናል፡፡ ይህ ሁሉ ተብሎ ግን ዶ/ሩ ዛሬ ባለ 614 ገፅ መፅሐፍ ቃሊቲ ውስጥ ፅፈው፣ ከቃሊቲ ወደ ማተሚያ ልከው እነሆ አቅርበውልናል፡፡ እንዴት ሆኖ? ወይ አያያዝ የተባለው ውሸት ነው፣ አሊያም መፅሐፉ የዶ/ር ብርሃኑ አይደለም፣ ወይም ቢያንስ ቃሊቲ አልተፃፈም፡፡ ይህን ማለት ግን ደግሞ ዶ/ር ብርሃኑን አለማመንና ውሸታም ማለት ይሆናል፡፡ መተፋፈግን ወይም የክፍል ጥበትን እንዲሁም የመተንፈስ ችግርን ከመፅሐፍ መፃፍ ጋር ምን አገናኘው? የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡ የሚያያዘው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡፡ ሀ/ይህን የሚያህል ፅሑፍ በመፅሐፍ መልኩ ለንባብ ለማብቃት ዶ/ር ብርሃኑ ብዙ ዋቢ ሰነዶችን ማገላበጥ አለባቸው፡፡ ይህንን እንኳን ድሮ አድርገው በመጨረስ በጭንቅላታቸው የያዙት ነው ብንል ይህን በፅሑፍ ለማስፈር በቂ ቦታ፣ ትኩረትን የሚያግዝ ፀጥታ እንዲሁም በቂ አየር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ታዲያ ይህን በቂ ቦታ፣ ይህን ፀጥታ እና በቂ አየር በዚያ የተፋፈገ የእስር ቤት ክፍል ውስጥ እንዴት አገኙ? ይህንንም አይ እንደውጭው ሁሉ በዚያች ክፍል ተፋፍጎ የሚገኘው ታራሚ ኢትዮጵያዊም እጅግ ስለሚወዳቸው ፅሑፉን እንዲፅፉ የሚያስፈልጋቸውን በቂ ቦታ አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርቦ በመቀመጥ ወይም በመተኛት ለቀቀላቸው፣ ተፈላጊውንም ፀጥታ በየተራ ዋርዲያ ቆሞ አስከበረላቸው ብለን ለማለፍ እንሞክር፡፡ አሁንም የማይታለፍ አንድ የተፈጥሮ ግዴታና እውነት አለ፡፡ ይህም ለ/በስነ ተፈጥሮ ሳይንስ እንደተቀመጠው (የ10 እና 11ኛ ክፍል ባዮሎጂ መፅሐፍ ሰርኩላቶሪ ሲስተም የሚለውን ያጤኗል) ከፍተኛ ትኩረትን እና የአእምሮ ጉልበት ማቃጠልን የሚጠይቅ ስራ የሚሰሩ ሰዎች በተፈላጊው ንቃትና ፈጣን የማሰብ አቅም ተግባራቸውን እንዲወጡ ከወትሮው የጨመረ የኦክስጅን መጠን ያስፈልጋቸዋል፡፡ እንግዲህ ዶ/ር ብርሃኑ መፅሐፉን ሲፅፉ አሉበት ወይም ነበሩበት የሚባለው ክፍል ይህን አይነት በቂ የኦክስጅን ስርጭት የማይፈቅድ መታፈንና ሽሚያ ያለበት ከሆነ ይህን የተፈጥሮ ግዴታ እንዴት ተወጡት? ዶ/ሩ የመተንፈስ ችግር ያለባቸው መሆኑ ሲታከልበት ደግሞ ጥያቄው ይበልጥ ይጠናከራል፡፡ በመሆኑም ዶ/ሩ ያሉበት ክፍል በቂ የኦክስጅን ስርጭት፣ ለመፃፍ የሚፈቅድ ቦታና ሁኔታ ያለበት ከመሆኑም በላይ አጋጠማቸው የተባለው የመተንፈስ ችግርም ቢያንስ ክብደቱ ያልከፋና በተደረገላቸው ህክምና ሊቀንስ ችሏል ከሚል መደምደሚያ ማምለጥ አይቻልም፡፡

በአጠቃላይ የዶ/ር ብርሃኑን መፅሐፍ በእርግጥም በዛሬዋ ኢትዮጵያ የነፃነት ጎህ መቅደዱን፣ ይህን ለመቀልበስ የተሞከረ ቢሆንም መቀልበስ እንዳልተቻለና በቀጣይም እንደማይቻል ከዋናው ባለ ጉዳይ የቀረበ ያገጠጠ ምስክርነት ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: ሁለት ውሸቶች እኩል እውነት አድርጎ የመጓዝን አስቸጋሪነትና የሚያስከትለውን እዳም ያመላከተ ጥሩ ዋቢ ነውና ደጋፊዎቻቸውም ሆነን ሌሎች የእውነትና የውሸት ብይኑን ሀቁን እየኖሩ ከሚገኙት ዶ/ር ብርሃኑ በላይ እንደማናውቀው አምነን ብንታረቅ እንደሚበጅ በራስ ምሳሌነት አመላክቶ ምክር ቢጤም ያስተላልፋል:: በዚህ አጋጣሚም መፅሐፉ ከቃሊቲ ተፅፎና ወጥቶ እያለ መንግስት ከገበያ ሊያግደው ነው በሚል የተያዘው ተራ ገበያን የማጦፍ ስልት አሳፋሪ መሆኑን ልጠቅስ እወዳለሁ:: መንግስት ፌስታል ገልጦ ማየት ፈርቷል ወይም ተስኖታል የሚል የቁጭ በሉ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር መፅሐፉ መታገድ ከነበረበት እንኳን በየመብራቱ ልናገኘው ይቅርና ቀድሞውኑ ከቃሊቲ መውጣት ቀርቶ በቃሊቲ ውስጥ እንዳይፃፍ በተከለከለ ነበር::

ለሁሉም ዶ/ር ብርሃኑ አስበውትም ይሁን ሳያስቡት ላበረከቱት መድኃኒት የሆነ ምስክርነት ምስጋናዬ ይድረሳቸው:: በነካ እጃቸው በመፅሐፋቸው ዙሪያ የሚታየውን የገበያ ድራማ «እባካችሁ ተዉ፣ በስሜ ብቻ ይሸጥላችኋል» ብለው አንድ ቅዳሜ ቢመክሩልን አደራ::

**(ምንጭ: ኢፍቲን ጋዜጣ - ነሀሴ 20/1998 ዓ/ም)**